www.abyssinialaw.com

14ኛ ዓመት ቁጥር 11
14th Year No 11

ባህር ዳር ነሐሴ 6 ቀን 2001 ዓ.ም
Bahir Dar 12th, August 2009

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ዝክረ-ሕግ

ZIKRE-HIG OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 28.22 Price Birr	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE	የፖ.ሣ.ቁ. 312 P.O.Box 312

ማውጫ	CONTENTS
ደንብ ቁጥር 69/2001 ዓ.ም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የከተሞች የገቢ አርዕስትና ታሪፍ መወሰኛ ክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ	**Regulation No. 69/2009** The Amhara National Regional State The Revised Cities' Revenue Title and Tariff Determination, Council of the Regional Government Regulation.

ደንብ ቁጥር 69/2001 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የከተሞች የገቢ አርዕስትና ታሪፍን ለመወሰን የወጣ ክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ

Regulation No. 69/2009

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE REVISED CITIES' REVENUE TITLE AND TARIFF DETERMINATION IN THE AMHARA

www.abyssinialaw.com

NATIONAL REGIONAL STATE.

የክልሉ ከተሞች ከፊዚካላዊ ልማት በተጨማሪ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትንም እንዲመሩ በሚበያስችላቸው ያልተማከለ አደረጃጀት ተዋቅረው የአካባቢ የራስ በራስ መልካም አስተዳደርና የነዋሪውን ሕዝብ ቀጥተኛ ተሣታፊነትን የሚያረጋግጥ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን በማስፈን ሂደት የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ የሚያስችላቸው የፖለቲካና የአስተዳደር ሥልጣንና ኃላፊነትን እንዲረከቡ አስቀድሞ በመደንገጉ፤

Whereas, it has been stipulated, in advance, that the Regional Cities are, having been structured in a decentralized structure that enables them to direct, in addition to their physical development, their social and economic development as well, to take over powers and responsibilities of politics and administration that enable them to play their role in the process of prevailing of democratic system that ensures local self-good governance and involvement of the city dwellers.

ከተሞች ከሕዝብ ቁጥራቸው መጨመር ጐን ለጐን የኢኮኖሚ አድማሳቸው እየሰፋ በሄደ ቁጥር የሚያስፈልጓቸውን ተጨማሪ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ የሚያስችላቸውን ገቢ በግብር፣ በቀረጥ፣ በአገልግሎት ክፍያ እና በሌሎች የገቢ ማመንጫ አርዕስቶች ከተገልጋዩ ሕብረተሰብ እንዲሰበስቡ ካላቸው ልዩ ባህርይ የተነሳ ኃላፊነት የተሰጣቸው ከመሆኑ በተጨማሪ በገቢ ራስን የመቻል መርህ አንግበው እየተንቀሳቀሱ የሚገኙ ቢሆንም የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችላቸውን ገቢ ከራሳቸው የገቢ አርዕስት እያገኙ ባለመሆኑ፣

Whereas, Cities, besides increasing their population size where their economic scope becomes wider and wider, in addition to that they are given a responsibility, as they have special characteristic to collect revenue enabling them to provide necessary additional socio-economic services in tax, dues, service charges and in other revenue sourcing titles form service seeking society, have not received from their own revenue titles an income that enables them to discharge duties and responsibilities given to them although they are acting with a principle of self-independence in revenue.

የታሪፍ ደንቡ በሥራ ላይ ከዋለ ከ8 ዓመታት በላይ ያስቆጠረ በመሆኑ ከወቅታዊ የአገልግሎትና የቁሳቁስ ዋጋ እድገት አኳያ ተመኑን ማስተካከል ተገቢ ስለሆነና አዳዲስ የገቢ አርዕስቶችንም

Whereas, since it has been over eight years since the Tariff Rate Regulation has been issued and enacted thereof, it is appropriate to adjust the tariff rate to the current service and the rise of price of materials

www.abyssinialaw.com

ያካተተ ሆኖ መውጣት እንዳለበት በመታመኑ፣

የታሪፍ ማሻሻያ ሲደረግ ገቢን ለማሳደግ ብቻ ሳይሆን ፍትሐዊ የሆነ፣ የግብር አሰባሰብን ይበልጥ ቀላል ለማድረግ፣ በንግድ እንቅስቃሴ ላይ ተፅዕኖ እንዳያስከትልና ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር ሊጣጣም በሚችል አግባብ ለማስተካከል እንዲሁም ከተሞች የራሳቸውን ታሪፍ የማውጣት ሥልጣንን በማይጋፋ መልኩ ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል የከተማ አስተዳደሮችና የማዘጋጃ ቤቶች የገቢ አርዕስትና ታሪፍ መወሰኛ ደንብ ቁጥር 69/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ፣

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚሁ ደንብ ውስጥ፦

1. "ግብር" ማለት አንድ ሰው ወይም ድርጅት ገቢ ሊያስገኝ በሚችል ሥራ ላይ ተሰማርቶ

and believed that the Tariff rate Regulation has to be issued comprising new revenue titles as well.

Whereas, while tariff rate is adjusted, it has been found necessary to adjust, not only to raise the revenue but to make fair tax collection more uncomplicated, not to make an impact on trade activity and to adjust it in harmony with variable changeable circumstances as well as not to override the power of cities to levy their own tariff rates thereof.

Now, therefore, the Council of the Amhara National Regional Government, by virtue of the powers vested in it under the provision of Art. 58 sub art. 7 of the revised national regional constitution, hereby issues this regulation.

PART ONE

1. Short Title

This regulation may be cited as "The Revised Amhara National Region City Administrations and Municipalities' Revenue Title and Tariff Determination, Council of Regional Government Regulation No.69/2002."

2. Definition

Unless the context otherwise requires, in this regulation:

1. "Tax" means a mandatory of payment to be imposed on the income of a person or an

www.abyssinialaw.com

በሚያገኘው ገቢ ላይ እንደ ገቢው መጠን የተወሰነ ድርሻ /መቶኛ እንዲከፍል በሕግ የሚጣል የክፍያ ግዴታ ነው፣

2. “የአገልግሎት ክፍያ /የመጠቀሚያ ክፍያ” ማለት አንድ ሰው ወይም ድርጅት ዕቃ/አገልግሎት ከከተማ አስተዳደሩ/ማዘጋጃ ቤቱ በመግዛቱ የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን ዋጋ እንደየፍጆታው መጠን ተሰልቶ እንዲከፈል በሕግ የሚጣል የክፍያ ግዴታ ነው፣

3. “መቀጫ” ማለት ደንቦችን በመተላለፍ የሚጣል ቅጣት ነው፣

4. “ኪራይ” ማለት ግለሰብ ወይም ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል የከተማ አስተዳደሩን /የማዘጋጃ ቤቱን ሃብትና ንብረት እንዲጠቀምበት በያዘው ይዞታ ለተጠቀመበት አገልግሎት በተከራዩ እና በከተማ አስተዳደሩ ወይም ማዘጋጃ ቤቱ መካከል በተደረሰው ውል መሠረት የሚከፍለው ክፍያ ነው፣

5. “የገቢ ታሪፍ” ማለት ከተማ አስተዳደሮች ወይም ማዘጋጃ ቤቶች በዚህ ደንብ መሠረት ገቢ ለሚሰበስቡባቸው አርዕስቶችና በእያንዳንዱ የገቢ ርዕስ የሚከፈላቸው የገንዘብ መጠን በቁርጥ ወይም በመቶኛ ተሰልቶ የሚደነገግበት ዝርዝር ነው።

6. “ቢሮ” ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ነው።

organization engaging in income generating activity to pay out fixed amount of share/percentage, according to the amount of his income against the income he generates thereof.

2. “Service Charge/ using charge” means a mandatory of payment to be imposed on a person or organization because he/it purchases goods/service from the city administration/municipality to pay out the value of goods/its services having been calculated against the amount of its consumption.

3. “Penalty” means a fine to be imposed on due to breaching regulations.

4. “Rent” means a payment that a person or an organ having legal personality could, on the basis of contract made between the lessor and the city administration or municipality, pay for the service he/it has obtained from the possession and property of city administration /municipality which it has owned to use it hereof.

5. “Revenue Tariff” means revenue title on which city administrations or municipalities shall, pursuant to this regulation hereof, collect revenue and a list on which amount of money to be paid for them, having been calculated against each revenue title in a lump sum or percentage and provided for.

6. “Bureau” means Bureau of Works and Urban Development of the Amhara National Regional State.

www.abyssinialaw.com

3. የደንቡ ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በአማራ ብሔራዊ ክልል ውስጥ በሚገኙ የከተማ አስተዳደር፣ የመሪና ንዑስ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች እንዲሁም ታዳጊ ከተሞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

3. Scope of Application

This regulation shall apply to cities of city administration, lead and sub-municipality as well as emerging cities of the Amhara National Region.

ክፍል ሁለት

ስለ ከተሞች የገቢ አርዕስት፣ የታሪፍ/ግብር አወሳሰን፣ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም

PART TWO

DETERMINATION OF TARIFF/TAX, REVENUE COLLECTION AND UTILIZATION OF REVENUE TITLES OF CITIES

4. ስለ ከተሞች ገቢና ታሪፍ አወሳሰን፣

1. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ማናቸውም የከተማ አስተዳደር፣ ማዘጋጃ ቤት እና ታዳጊ ከተሞች ከተገልጋዩ ሕብረተሰብ ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ ግብር፣ ቀረጥ እና የአገልግሎት ክፍያዎችን በዚህ ደንብ መሠረት በሠንጠረዡ በተመለከቱት የገቢ ማመንጫ አርዕስቶች ላይ በትይዩ የተመለከተው ታሪፍ መነሻ እና ጣሪያው እንደተጠበቀ ሆኖ እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ታሪፎቻቸውን በመወሰን ገቢ ሊሰበስቡ ይችላሉ፣
2. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የሰፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከተሞች ከሃብትና ንብረት ኪራይ እንዲሁም ሽያጭ

4. Determination of Revenue and Tax of Cities

1. Any city administration, municipality and emerging cities in the Region may, having determined their tariff as the objective situation of locality, without prejudice to the minimum and maximum ceiling tariff rates indicated in parallel on revenue sourcing titles as indicated in the table, pursuant to this regulation, collect revenue of monthly or yearly taxes, dues and service charges from the service seeking society.
2. Without prejudice to the provision of sub.art.1 of this article hereof, cities shall have powers to administer the revenue obtained

www.abyssinialaw.com

የሚያገኙትን ገቢ የማስተዳደር ሥልጣን ይኖራቸዋል።

3. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው ቢኖርም ማናቸውም የከተማ አስተዳደር እና ማዘጋጃ ቤት ከተሞች ከግለሰቦች መንግስታዊ ከሆኑና ካልሆኑ ድርጅቶች የሚቀርቡ የዓይነትና የጥሬ ገንዘብ ስጦታዎችን/ድጋፎችን መቀበል ይችላሉ።

5. ስለ ከተሞች የገቢ አርዕስት

1. ማናቸውም የከተማ አስተዳደር፣ የማዘጋጃ ቤት እና ታዳጊ ከተሞች በዚህ ደንብ መሠረት ከተገልጋዩ ህብረተሰብ የአገልግሎት ማስፈፀሚያ ክፍያ፣ ግብር ቀረጥ የሚጥልባቸውና ገቢ የሚሰበስብባቸው የገቢ ማመንጫ አርዕስቶች የዚህ ደንብ አካል ሆኖ በተያያዘው አባሪ ላይ ከከተሞቹ ደረጃ ና ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ተለይተው በተመለከቱት መሠረት ይሆናል።

2. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ከተሞች ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ሲያቀርቡ የአገልግሎት መጠቀሚያ ክፍያዎችን ተመን በማውጣት የመጠየቅ ሥልጣን ይኖራቸዋል።

   ሀ/ የከተማ አስተዳደሮች ወይም ማዘጋጃ ቤቶች የራሳቸውን የአገልግሎት መጠቀሚ ክፍያ ተመን በማውጣት ክፍያ የሚጠይቁባቸውን የአገልግሎት ዘርፎችን እንደየከተሞቻቸው ተጨባጭ

from rent of resource and property as well as from sales.

3. Notwithstanding the provisions of sub. Art. 1 and 2 of this article hereof, any city administration and municipality city may receive donations/ supports, in kind and in cash, granted from individuals, governmental and non-governmental organizations.

5. Revenue Title of Cities

1. The revenue sourcing titles on which any city administration, municipality and emerging cities may, pursuant to this regulation hereof, impose service execution charges, taxes and dues and collect revenue from service seeking society shall be on the basis of those specifically indicated with regard to class and objective situation of each city annexed under this regulation therewith.

2. Notwithstanding the provision of sub.art.1 of this article hereof cities shall, having assessed their tariff rates, have the power to request service charges where they provide various services therewith.

   A. City administrations or municipalities shall, having assessed their own service using charge rates, determine themselves service sectors on which they may request a charge depending upon objective situation of their

www.abyssinialaw.com

ሁኔታ በራሳቸው ይወስናሉ።

ለ/ ከተማ አስተዳደሮች ወይም ማዘጋጃ ቤቶች ከአገልግሎት መስጫ ፕሮጀክቶች ጋር የተያያዙ የካፒታል፣ የጥገና ወጪዎችን ጨምሮ የሥራ ማስኬጃ ወጪውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሚመልሱ የአገልግሎት መጠቀሚያ ክፍያ ታሪፎችን እንደአስፈላጊነቱ (ማለትም አገልግሎቱን ማቅረብ እንደተጀመረ ወይም በአገልግሎት መስጫ ተቋማቱ ላይ ዕድሳት ከተደረገ) በተጠቃሚዎች የመጣል ወይም ተመኑን የማሻሻል ሥልጣን አላቸው፣

ሐ/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር የተደነገገው ቢኖርም ማናቸውም ከተማ አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤት በተደራጀበት ከተማ ክልል የሚመድበውና የሚሰበስበው የአገልግሎት ክፍያ ለነዋሪው ሕዝብ ከሚያቀርቡት የአገልግሎት ዓይነትና ጥራት/ደረጃ ጋር መመጣጠን ይኖርበታል።

3. ከተማ አስተዳደሮች ወይም ማዘጋጃ ቤቶች ከሃብትና ንብረት ኪራይ የሚሰበሰብ ገቢን በተመለከተ እራሳቸው በሚይዙት የውል ስምምነት መሠረት ይሆናል።

ሀ/ ማናቸውም የከተማ አስተዳደር እና

cities.

B. City administrations or municipalities shall, as deemed necessary (as soon as the provision of the service is commenced or if maintenance is made on the service delivery institution), have the power to impose tariffs of service using charges to be, fully or partly, refund capital, including to maintenance, and working capital expenditures which are related to service delivering projects on beneficiaries or adjust the rate thereof.

C. Notwithstanding the provision of sub. Art. 2 of this article hereof, service charges to be levied and collected in urban center limit where any city administration or municipality is organized thereof, shall be equivalent to the type and quality/standard of services it renders to the urban dwellers.

3. with regard to an income to be collected form rent of resource and property of city administrations or municipalities, it shall be on the basis of contractual agreement they may enter into thereof.

A. In any city in which city administration and municipality is established thereof, they shall

www.abyssinialaw.com

ማዘጋጃ ቤት በተቋቋመበት ከተማ በሊዝ ወይም በማናቸውም የኮንትራት ውል ስምምነቶች ያስላተለፏትን የቋሚ ንብረት እንዲሁም በኪራይ መሬት ይዞታ ስሪት የተያዘ የከተማ ቦታ ዋጋ ዕድገት (advalorum tax/betterment levy) የመጣል ሥልጣን ይኖራቸዋል።

ለ/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3.ሀ ሥር የሰፈረው ድንጋጌ በሊዝ የመሬት ይዞታ ስሪት የተያዘ ወይም የተላለፈ ቦታን አይመለከትም።

4. ከንቲባው ወይም የማዘጋጃ ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ከዚህ ደንብ ጋር በአባሪነት በተያያዘው ማዕቀፍ መሠረት የራሳቸውን ታሪፍ፣ ከሃብትና ንብረት ኪራይ ስለሚሰበሰብ ገቢ፣ የውል ስምምነት እንዲሁም የአገልግሎት ክፍያ ተመን በማዘጋጀት እንደየአግባቡ ለከተማው ወይም ለወረዳው ም/ቤት ይሁንታ ማቅረብ ይኖርበታል።

6. የንግድ ሥራና የሙያ አገልግሎት ግብር አወሳሰን

1. በማናቸውም የከተማ አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤት የገቢ አሰባሰብና ክትትል የሥራ ሂደት በከተማው ክልል በንግድ ሥራ ላይ የተሠማራን ወይም የሙያ አገልግሎት የሚሰጥን ማናቸውንም ግለሰብ ወይም መንግስታዊ የሆነና ያልሆነ የልማት ድርጅትን በየከተሞች ወቅታዊ መረጃወችን

have the power to impose advalorum tax/ betterment levy on the fixed asset which have transferred thereto through lease or in any contractual agreements as well as on urban land holding held in rental land holding system.

B. The provision under sub. Art. 3(A) of this article hereof shall not include the land holding held or transferred through land leasehold system.

4. The mayor or manager of the municipality shall, pursuant to the framework annexed under this regulation therewith, prepare their own tariff, income to be collected from rent of resource and property, contractual agreement as well as service charge rates and thereby submit same to their respective city or woreda council for the approval.

6. Determination of Trade and Professional Service Tax

1. The Income Collection and Follow-up Work Process in any city administration or municipality shall, by collecting and recording current information in each city and evaluating same with respect to the weighting criterion indicated herein below, determine annual trade activity and

www.abyssinialaw.com

በመሰብሰብና በመያዝ ዝቅ ብሎ ከተቀመጠው መመዘኛ መስፈርት አኳያ እየገመገመ ለደረጃው የሚመጥን ዓመታዊ የንግድ ሥራና የሙያ አገልግሎት ክፍያ ይወሰናል።

2. ለግብር አወሳሰን ያመች ዘንድ ማናቸውም ጅምላ ነጋዴ የንግድ ፈቃዱን ባወጣበት ከተማ መጋዘኑን የማሳየት ግዴታ አለበት፣

3. ለእያንዳንዱ የንግድ ዘርፍ በመመዘኛ መስፈርቱ መሠረት በሚገኘው ድምር ውጤትና ይሄን መሠረት አድርጎ በሚሰጠው ደረጃ መሠረት ግብር የሚጣልበት ቢሆንም አስፈላጊ ባልሆነ መንገድ ተጠቃሚ ለመሆን የሚሞክሩ ነጋዴዎች ላይ ተፅዕኖ ለማሳረፍ ሲባል ከሕብረተሰቡ የሚገኙን ሌሎች መረጃዎችንም ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ እንደገና ደረጃ ሊወጣለት ይችላል፣

4. አንድ ነጋዴ ስለሚያከናውነው የንግድ ዘርፍ ዓመታዊ ሽያጩንም ሆነ ለድርጅቱ ያፈሰሰውን የካፒታል ልክ ስሌት የንግድ ፈቃዱን ባወጣበት ከተማ ታሣቢ ይደረጋል፣

5. የንግድና የሙያ አገልግሎት ሰጪዎች የደረጃ ምደባ ለሕዝብ ምርመራ ክፍት

professional service charges, equivalent to the grade, on any individual or governmental and non-governmental development organization in the urban center limit engaging in trade activity or rendering professional service.

2. In order to be favorable for determination of tax, any wholesaler shall have the duty to show his storehouse in the city whereabouts he has been licensed.

3. Although a tax is imposed on each trade sector on the basis of sum total of weighting criteria and grade to be set to it based on this, so as to make impact on merchants who may try to be beneficiary in an improper way, a grade may be re-set in the manner of taking into account other information obtained form the society.

4. Calculation of annual sale as well as actual amount of capital invested on the trade sector which a merchant runs thereof shall be in consideration of the city whereabouts he is licensed.

5. Grade category of trade and professional service providers shall be publicized for public review.

www.abyssinialaw.com

መሆን አለበት።

6. ግብር ከፋዩ የተለያዩ እና ከአንድ በላይ የንግድ ዘርፎች ያሉት ሆኖ ከተገኘ ለእያንዳንዱ የንግድ ዘርፍ በመስፈርቱ መሠረት የሚደርስበት ዓመታዊ ግብር በተናጠል ከተሰላ በኋላ የድምር ውጤቱን እንዲከፍል ይደረጋል።

6. Where it is found that the tax payer has owned various and more than one business sectors, he shall be made to pay the sum total of each trade sector after it has individually been calculated the annual tax rates of each business sector entitles to him, pursuant to the criterion.

7. ስለ ከተሞች ገቢ አሰባሰብ

1. የከተማ አስተዳደሮች ወይም ማዘጋጃ ቤቶች በዚህ ደንብ ከተያያዘው ዘንጠረዥ ጋር የተመለከተውን ዓመታዊ የንግድ ሥራና የሙያ አገልግሎት ግብር በሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች እያስወሰኑ በየበጀት ዓመቱ እስከ ግንቦት 30 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ገቢ ይሰበስባሉ፣

2. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የሰፈረው ድንጋጌ ከተማ አስተዳደሮች/ ማዘጋጃ ቤቶች ለሚሰበስቧቸው ለማንኛውም የአገልግሎት ክፍያዎችም በተመሳሳይ ይፈፀማሉ፣

3. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ሥር የከተማ አስተዳደሮች ወይም ማዘጋጃ ቤቶች ከተገልጋዩ ህብረተሰብ የሚሰበስቧቸውን ግብር፣ ቀረጥና የአገልግሎት ክፍያዎች በወቅቱና በአግባቡ አስከፍለው ለአስፈላጊው አገልግሎት በማዋል ረገድ በተዋረድ ቀበሌዎች አፈፃፀሙን ከመደገፍና ከመተባበር ባሻገር ተለይቶ በሚሰጣቸው የገቢ ታሪፍ መሠረት ገቢ የመሰብሰብ ኃላፊነት እና ግዴታ አለባቸው።

7. Income Collection of Cities

1. City administrations or municipalities hall, having caused the determination of them by pertinent work heads, collect revenues from annual trade activity and professional service tax indicated in the table annexed under this regulation therewith up to may 30 in the fiscal year.

2. The provision stipulated under sub. Art. 1 of this article shall also apply to any service charges to be collected by city administration or municipalities.

3. With respect to using tax, dues and service charges that city administrations and municipalities may, having caused them to be paid timely and properly, collect from service seeking society pursuant to the provisions under sub. Art. 1 and 2 of this article hereof, kebeles at all hierarchy shall, in addition to supporting the implementation and cooperating, have duties and responsibilities to collect revenue on the basis of revenue tariff specifically given to them.

www.abyssinialaw.com

8. ስለ ገቢ አጠቃቀም እና ዘገባ

1. ማናቸውም የከተማ አስተዳደር እና ማዘጋጃ ቤት ከተሞች በየደረጃው ለተቋቋመው ምክር ቤት ያለው ተጠሪነት እንደተጠበቀ ሆኖ በዚሁ ደንብ መሠረት የሚወሰነውና የሚሰበሰበው ገቢ ለተከማው ነዋሪ ሕዝብ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ እና የመሠረተ ልማት ማስፈፀሚ የማዋል ኃላፊነትና ግዴታ ይኖርበታል፣
2. ማናቸውም የከተማ አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከተገልጋዩ ሕብረተሰብ የተሰበሰበውን ገቢ ለታለመለት ዓላማ ያዋለው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥና በመረጃዎች የተደገፈ ወቅታዊ ሪፖርት ለነዋሪው ሕዝብና በየደረጃው ለሚገኝ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት እና ም/ቤት የማቅረብ ግዴታ አለበት።

8. Utilization and Report of Income

1. Any city administration and municipality cities shall, without prejudice to their accountability to the council established as every level, have duty and responsibility to spend the revenue to be levied and collected, as per this regulation, on the execution of socio-economic and infrastructure development to the urban dwellers.
2. Any city administration or municipality is duty bound to submit a timely report, with supporting documents and that ensures that revenue collected from service seeking society in the fiscal year is invested on the desired objective, to the urban dwellers and to the finance and economy development office and to the council at all level.

ክፍል ሦስት

በግብር አወሳሰን ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ፣ የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓትና የውሣኔ አፈፃፀም

PART THREE

GRIEVANCE LODGED AGAINST TAX DETERMINATION, GRIEVANCE SUBMITTAL PROCEDURE, AND EXECUTION OF DECISION

9. በግብር አወሳሰን ላይ ስለሚቀርብ

9. Grievance lodged Against Tax

www.abyssinialaw.com

ቅሬታና የአቀራረብ ሥነ-ሥርዓት

1. እያንዳንዱ ከተማ በመመዘኛ መስፈርቱ መሠረት ወቅታዊ መረጃዎችን በመያዝ የግብር ከፋዮችን ደረጃ ሲያወጣ ወይም በማንኛውም ግብር አወሳሰን ሂደት ግብር ከፋዮች ቅሬታ ካቀረቡ /ይግባኝ ካሉ/ ይግባኙን የሚመረምርና ውሣኔ የሚሰጥ ገለልተኛ የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ይኖረዋል።
2. በገቢ አሰባሰብና ክትትል የሥራ ሂደት ውሣኔ ቅር የተሰኘ ማናቸውም ግብር ከፋይ እንዲከፍል ከተወሰነበት ግብር ውስጥ 50 በመቶውን በቅድሚያ አስይዞ ውሣኔ በጽሑፍ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ በደረጃው ለተቋቋመው የግብር ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው።
3. የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴው በተመለከቱት ክፍያዎች መጠን ላይ ይግባኙን የመመርመርና ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን ይኖረዋል።
4. ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴው አቤቱታው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ተገቢውን ማጣራት አድርጐ የገቢ አሰባሰብና ክትትል የሥራ ሂደት ውሣኔን የመሻር የማፅናት ወይም እንደአስፈላጊነቱ ውሣኔውን የማሻሻል ሥልጣን አለው። መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ካልሆነ በስተቀር የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል።

Determination and its Submittal Procedure

1. Each and every city shall have impartial Grievance Hearing Committee that reviews and makes decision on the appeal if tax payers lodge grievance/if they appeal/ in any tax determination process or where it sets grades of tax payers by recording current information, in accordance with the weighting criterion.
2. Any tax payer who is aggrieved by the decision of Revenue Collection and Follow-up Work Process shall, prior submission of 50% of the tax imposed on him as guarantee, have the right to lodge complaint to the Tax Appeal Hearing Committee established at all level within thirty days for the date the decision is communicated to him.
3. The Appeal Hearing committee shall have the power to review the appeal and make a decision on the charge rate determined thereof.
4. The Tax Appeal Hearing Committee shall, having made proper review within thirty days from the date the compliant is communicated to it, have the power to reverse, affirm or, as deemed necessary, amend the decision of the Revenue Collection and Follow-up Work Process. The decision of the Appeal Hearing Committee shall be final unless there shall

www.abyssinialaw.com

be basic legal errors.

10. የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ አወቃቀርና አሠራር

የግብር ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴዎች አወቃቀርና አሠራር የከተሞችን ደረጃ ባገናዘበ መልኩ በመመሪያ ይወሰናል።

10. Structure and Working Procedure of the Tax Appeal Hearing Committee

Structure and working procedure of the tax appeal hearing committee shall be determined by a directive in a manner of conforming with cities' grade thereof.

11. የውሣኔ አፈፃፀም

1. በማናቸውም የከተማ አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤት የገቢ አሰባሰብና ክትትል የሥራ ሂደት እና ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴው በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 4 መሠረት የሰጡት የግብር ውሣኔ በግብር ከፋዩ እንቢ.ተኝነት ወይም ግድየለሽነት አለመፈፀሙ ሲረጋገጥ አግባብ ባለው የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት አቅርቦ ይወሰናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ለማህበራዊ ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ፍትሐብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን እስካላለፉ ድረስ በአዋጅ ቁጥር 151/2000 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ መሠረት አግባብ ላላቸው ማህበራዊ ፍ/ቤቶች እየቀረቡ ይፈፀማሉ።

11. Execution of Decision

1. Where it has been ascertained that the decision of tax made by the Revenue Collection and Follow-up Work Process of any city administration and municipality and by the Appeal Hearing Committee pursuant to sub. Art. 2 and 4 of art. 9 of this regulation hereof could not be executed due to the disobedience or negligence of the tax payer, it shall be submitted to the relevant civil code procedure law and decided thereon.
2. Notwithstanding the provision stipulated under the provision sub. Art. 1 of this article, it shall be presented to the relevant social courts in accordance with sub. Art. 1(A) of article 12 of the proclamation No151/2008 (as amended) unless it exceeds the jurisdiction of civil code given to social courts.

www.abyssinialaw.com

3. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የሥራ ሂደቱ የግብር ማስታወቂያ በደረሳቸው በ30 ቀናት ውስጥ ተፈላጊውን ክፍያ ያልከፈለ ወይም በተደነገገው መሠረት ቅሬታ አቅርበው አግባብ ባለው አካል ታይቶ ወሣኔ ከተሰጠው በኋላ በውሣኔው ካልተስማሙ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ጉዳዩን ማቅረብ ባለባቸው ጊዜ ሳያቀርቡ በመቅረት የግብር ግዴታቸውን ያልተወጡ ግብር ከፋዮችን ሃብትና ንብረት በማስከበር/በመያዝና በመሸጥ ለዕዳው ማካካሻ ማዋል ይችላል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

12. ቅጣት

ማናቸውም የከተማ አስተዳደር ወይም ማዘጋጃ ቤት ይህን ደንብ መሠረት በማድረግ የወሰነውን ግብር ወይም እንዲከፈል ያዘዘውን ክራይ፣ ቀረጥም ሆነ የአገልግሎት ክፍያ በቂና ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖረው በወቅቱ ለመክፈል የታቀበ እንዲሁም ሌሎችን ያነሳሳ ማናቸውም ሰው አስቀድሞ የተወሰነበትን እዳ በሕጋዊ የባንክ ወለድና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ከተመለከቱት ቅጣቶች ጋር መክፈሉ ሳይቀር አግባብ ባለው ሕግ ይቀጣል።

3. Without prejudice to the provisions of sub. Art. 1 and 2 of this article hereof, the Work Process may, having suspended/ held and sold resource and property of those tax payers who has failed to discharge their tax obligation because they failed to submit the matter to juridical court in a specified period of time they have to do so if they disagreed on the decision after they have lodged a grievance and it is given a decision, having been reviewed by the pertinent body pursuant to the provision stipulated thereof or of those who has failed to pay tax charge required from them within thirty days from the date the tax notification is communicated to them, compensate same for its loan. The detail shall be determined by a directive.

12. Penalty

Any person who has declined to pay timely, with no good cause and legal grounds, and who has instigated others not to pay the tax that any city administration or municipality has determined, pursuant to this regulation, or rent, dues as well as service charges it has ordered him to pay shall, without prejudice to the payment of the tax that is pre-determined on him at the rate of legal bank interest and penalties indicated in the table annexed under this regulation therewith, be fined in accordance with relevant law.

www.abyssinialaw.com

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሊያወጣ ይችላል።

14. ደንቡን ስለማሻሻል

ይህ የከተሞች የገቢ አርዕስት እና ታሪፍ ማሻሻያ ደንብ ልዩ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር ቢዘገይ በየአምስት ዓመቱ ሊከለስ ይችላል።

15. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጐች

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የማዘጋጃ ቤቶች የገቢ ማሻሻያ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ደንብ ቁጥር 12/1992 ዓ.ም እና ደንብ ቁጥር 20/1996 ዓ.ም እንደተሻሻለ በዚህ ደንብ ተሽረዋል፣

2. ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብና መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

16. ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

PART FOUR

MISCELLANEOUS PROVISIONS

13. Power to Issue Directive

The Regional Bureau of Works and Urban Development may issue directives necessary for the implementation of this regulation.

14. Amendment of the Regulation

The Revised Cities Income Title and Tariff Regulation may, unless and otherwise special circumstances happened thereof, be revised not later than every five years.

15. Inapplicable Laws

1. The Revised Tariff of Municipalities, Executive Committee Regulation No.12/1999 of the Amhara National Regional State and the Regulation No.20/2004 (as amended) has been repealed by this regulation.

2. Any other law, regulation and directive or customary practice inconsistent with this regulation shall not apply to matters provided for in this regulation.

16. Effective Date

This regulation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre-Hig Gazette of the Regional State.

www.abyssinialaw.com

ባህር ዳር

ነሐሴ 6 ቀን 2001 ዓ.ም

አያሌው ጐበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር

Done at BahirDar

This 12th day of August, 2009

Ayalew Gobezie

Head of Government of the Amhara

National Regional State